# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 5 ቁጥር 3 ሚያዝያ 16 ቀን 2013 ዓ.ም.


## ሁሉም አማራ ለአንድ ኢትዮጵያ

በተቀነባበረ ተንኮል ልትጠፋ የማትችለውን ኢትዮጵያ የማጥፋት ዘመቻው በብልጽግና መንግሥት ደረጃ ተጧጡፏል። ኢትዮጵያን ማጥፋት ማለት ኢትዮጵያን በወራሪ መቃብር ላይ ሀገር ያደረጓትን የምኒልክ ታሪክ ማጠልሸት ነው። በመንግሥት ደረጃ የተደገፈ ታሪክ አጉዳፊ ሀውልት ሲሰራ አይተን ዝም ብለናል። ቀዳማይ የክርስትና ሃይማኖት ተቀብላ የኖረችን ጥንታዊት ኢትዮጵያ፣ የእስልምና ሃይማኖትን ተቀብላ ያስተናገደች ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን፣ ሁሉንም እንደ እምነቱ አቻችላ የተጓዘች ኢትዮጵያን ለማጥፋት ተፈርጆ አይተናል። ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ላይ ከተዘመተ እነሆ 30 ዓመት ሆኖታል። ከዛሬ 30 ዓመት በፊት በአርባ ጉጉና በበደኖ የተጀመረው የዘር ማጥፋት ውስጥ ውስጡን እንደ ምስጥ ኢትዮጵያንና ትውልዱን እየበላ እነሆ ዛሬ ሰው አራጅ ዘማች ጽንፈኞች አብቅላለች። ለዚህም ከፍተኛውን የሕይወት እልቂት ድርሻ እያስተናገደ ያለው አማራው ሲሆን ከእነ መኖሪያው እየጋየ፣ እየተገደለ ነው። እናቶች፣ አባቶች፣ ሕጻናት፣ ወጣቶች እየተጨፈጨፉ ነው። ቀያቸውን ትተው የተሰደዱትም በረሃብ፣ በጥማት፣ በበሽታ እያለቁ ነው።

አድማሱን እያሰፋ የመጣው የአማራ እልቂት የዛሬ 30 ዓመት የተቀበረው የወያኔ/ኢሕአዴግ ፈንጂ ሕገ መንግሥት ውጤት ነው። ሕገ መንግሥቱን ከለላ አድርጎ ሀገርና ትውልድ ሊቀብር ውጥኑ የነበረው ወያኔ/ህወሓት ተቀበረ የምንለው ያለምንም ማመንታት ዘረኝነትና ሕገ መንግሥቱ ሲቀበር ነው። የወያኔ ሕገ መንግሥት የመጨረሻው ደረጃ ሀገር ማጥፋት እንደሚሆን ከ30 ዓመት በፊት ተነግሯል። በአለፉት 3 ዓመት በለውጥ ስም ፍላጎቱን ለማሟላት ታጥቆ የተነሳው የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐብይ አገዛዝ ገና ከጅምሩ "ሕገ መንግሥቱን ተገን አድርጌ ለውጥ አመጣለሁ" ሲለን መስማት፣ ማድመጥ ያቃተን እኛው ነን። የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት በአንድ ዘር የበላይነት በህወሓት መሪነት አማራው፣ ኦርቶዶክስና ኢትዮጵያ ላይ በማነጣጠር ኢትዮጵያን አድቅቆ መበታተን ነበርና ኢትዮጵያ ሳትበታተን እራሱ ጉም ሁኖ በነነ። የ"ኢትዮጵያ" ቃል ከ27 ዓመት በኋላ መጠራት ብቻውን ለናፈቀን የወያኔ ሕገ መንግሥት አልታይ ብሎን የትላንት "የቀን ጅብ የሰው ጅብ" ሆኖ መጥቶብናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አሕመድ ገና ስልጣኑን እንደጨበጡ በለገጣፎና በቡራዩ የተጀመረው አዲስ አበባ ላይ ያነጣጠረ የቁሮ ጥቃት ዘመቻ በአዲስ አበባ ወጣቶች ምላሹ ቀላል አልነበረምና የዘር ፍጅቱ ከዳር ወደ መሃል ይጓዝ ዘንድ ኢትዮጵያዊነትን እየለፈለፉ ሲያዘናጉን ከበስተጀርባ ያሉት የሳሉትን ገጀራና ቆንጨራ የሰው ልጅ ላይ፣ አማራው አንገት ላይ አሳረፉት። ለገጣፎ ነዋሪ ሲፈናቀል "አልሰማሁም" ያለን መሪ፣ ቡራዩ ሲወረር ተከላካይ ወጣቶችን በማሰር ምላሽ ሲሰጠን፣ መላ አዲስ አበባ በ"ፊንፊኔ ኬኛ" ወራሪ ልትመሰቃቀል ሲነጣጠርባት አላስነካም ባዮች እነ እሥክንድር ነጋ ወደ እሥር ሲታጎሩ ማስተዋል ተሳነን። የግፉ መጠን ግዝፈቱ ችግኝ እየተከለ ሰው ሚነቅል መሪ ሰጠን።

ፓርክ እየገነባ ሻሸመኔን፣ መተከልን፣ አጣዬን አውዳሚ ለውጥ አሳየን። "ገበታ ለሀገር" እየተሰበሰበ አራጅ በዘመናዊ መሳሪያ አስታጥቆ አማራ ማስጨረስ ምላሻችን ሆነ።

ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ደርሳለች። መንደርና ሕዝብን በመፍጀት ሀገር ሚያጠፋ አገዛዝ መቀበሪያው ተቃርቧልና የጥፋት እጁ ረዝሟል። የወያኔ/ህወሓት አወዳደቅና አቀባበር ሊማር ያልቻለ ወይም ያልፈለገ አገዛዝ መቃብሩን እየቆፈረ ይገኛል። ኢትዮጵያ የወያኔን ሕገ መንግሥትና ዘረኝነትን ቀብራ ዳግም ምታብብበት ትንሳዔዋ ሕይወት ያስከፍል ይሆናል እንጂ ከቶም አትበታተንም።

ሰሞኑን በሀገሪቷ በተለይ በአማራው ኅብረተሰብ ዘንድ የተነሳው ሕዝባዊ ቁጣ ሊደገፍ የሚገባው የኢትዮጵያ መዳኛ ነው። "በቃን!" ግድያ ብቻ ሳይሆን "በቃን! የወያኔ ሕገ መንግሥት፣ በቃን! ዘረኝነት፣ በቃን! ዘርና ቋንቋን ያማከለ አከላለል" ያልን ጊዜ ኢትዮጵያን አዳናት፣ የ"በቃን!" እንቅስቃሴም ግቡ ሊሆን የሚገባው ይኸው ነው። ወያኔ/ህወሓት በትግራይ ሕዝብ ስም ዘረኝነትን ተክሎ፣ ትውልድ አምክኖ ሊሰጠን የሞከረውን የ100 ዓመት የቤት ሥራ ጥሎት ተቀበረ የምንለው ኢትዮጵያን አውዳሚው ሕገ መንግሥት ሲሻሻል አይደለም ሲቀበር ነው። በቀጣይነት የዘር ተረኝነት ውስጥ የገባው የኦነግ እና የኢሕአዴግ የበኩር ልጅ ብልጽግና በኦሮሞ ኅብረተሰብ ስም መንደር ማውደም፣ አማራን መጨፍጨፍ፣ ቤተ ክርስቲያን ማቃጠል ተግባሩ ያደረገ አሸባሪ ቡድን የመጨረሻው ምዕራፉ ላይ ደርሷልና "በቃን!" እንቅስቃሴ አቅጣጫውን መቃኘት እንዳለበት ልንጠቁም እንወዳለን።

በግልጽ እንጻፍ ከተባለ አማራው ለኢትዮጵያ የሞተላት ጥንት ነው። አማራ ሀገሩ ኢትዮጵያ ናት። አማራ ስንል በአማራ ክልል ያለውን ብቻ ሳይሆን በሁሉም ሀገሪቷ ክፍሎች ያሉትን አካቶ በተለይ በከተሞች የሚኖረው ዘሩን የማያውቅ፣ የዘር ቅኝት የሌለው፣ በኢትዮጵያዊነታቸው የሚኮሩ ዜጎችን ሁሉ ያጠቃልላል። አማራው "በቃን!" እንቅስቃሴ እራሱን ከመከላከል አልፎ ኢትዮጵያን ለማዳን መሆን ይኖርበታል። የሚከፈለውን መስዋዕትነት ከፍሎ በኦሮሞ ሕዝብ ከሚነግዱ የቀን አውሬዎች፣ ገዳዮች ኢትዮጵያን ነጻ ማውጣት ይኖርበታል። "ወያኔና ኦነግ ይተያያል ካብ ለካብ" እንዲሉ የኢትዮጵያ አምላክ የወያኔ/ህወሓትን አስኳል በሌላው ዘረኛ ቀብሮልናልና "በቃን!" እንቅስቃሴ ዘረኝነትን ለማብቀል ሳይሆን ለመቅበር ***"ሁሉም አማራ ለአንድ ኢትዮጵያ"*** መሪ መፈክሩ ማድረግ ይኖርበታል እንላለን።

"ኢትዮጵያ አትፈርስም!" ስንል ኢትዮጵያ ሀገራቸው የሆኑ ሲዳማዎች፣ ወላይታ፣ ጉራጌ፣ ጋምቤላ፣ ሀረሬ፣ አደሬ፣ ሱማሌዎች፣ አፋር፣ ቤኒ ሻንጉል፣ ወዘተ መቃኘት ይገባናል። ኢትዮጵያ ያለ ትግራይ ሕዝብ ያለ ኦሮሞ ሕዝብ ኢትዮጵያ አይደለችምና የአማራው መደራጀትና መንቀሳቀስ የወያኔ/ኢሕአዴግ ሕገ መንግሥትንና ዘረኝነትን በመቅበር ኢትዮጵያን ማዳን ሊሆን ይገባዋል እንላለን። ዛሬ በሀገራችን በተለይ በአማራው ላይ እየተካሄደ ላለው የዘር ፍጅት ተጠያቂዎች ለፍርድ ይቅረቡ ስንል ከአገዛዙ መጀመር ይኖርብናል። "በቃን!" እንቅስቃሴ ኢትዮጵያን የማዳን ተልዕኮውን ለመወጣት ዘረኞች፣ አሸባሪዎች፣ ወንበዴ መንግስት ጨፈጨፈ ተብሎ ምስኪን ወገኖችን ያገለለ ድርጊት ውስጥ ከተዘፈቀ የወያኔ/ህወሓት የአሁኑም ኦነግ/ብልጽግና ተልዕኮ ተሳካ ማለት ነው። የዚህ ጊዜ ነው ለማንም የማትሆን ኢትዮጵያ በአሳዛኝ ትርምስ ውስጥ የምትዘፈቀው። በመሆኑም አድምቀን ልናሰምርበት የምንፈልገው ***በሀገራችን ጭፍጨፋውና ሰቆቃው አማራው ላይ እጅጉን ቢበዛም አማራው የአማራን ክልል አስጠብቄ እፎይታ አገኛለሁ ከሚል ስህተት በመጽዳት ጥንትም በዐድዋ፣ በማይጨው የከፈለውን ሀገር አድን መስዋዕትነት በመድገም አደረጃጀቱን አጠናክሮ ኢትዮጵያን ከዘረኝነትና ከወያኔ***

***<u>አውዳሚ ሕገ መንግስት ነጻ ለማውጣት እይታውን ማስፋት ይኖርቢታል እንላለን።</u>*** “አራጆቹ” አሁን በአማራው ላይ የተቃጣው የዘር ማጽዳት ጭፍጨፋ ቢሳካላቸው በዚህ ያበቃል የሚል ግምት እንዳይኖረን። አድማሱን እያሰፋ የመጣው ውድመት አዲስ አበባን ከነነዋሪዋ ለማጥፋት የተወጠነ ጉዞ አካል ነው። ጉዞው ሕዝብ ለመጨረስ፣ ሀገርን ለመበታተን የተወጠነ የአሸባሪዎች ውጥን መሆኑን ተረድቶ አማራው ችሎታውም አቅሙም አለውና ኢትዮጵያን በማዳን በደምና አጥንቱ ዳግም ማንነቱን ማስመስከር ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ “ልባል እንጂ ነፍጠኛ ለሀገሬ አልተኛ” ብሎ “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! አንድ ሰንደቅ ዓላማ ለኢትዮጵያ” ብሎ በደሙ ታሪክ የሚሠራበት ወቅት ላይ ደርሷልና ***<u>“ሁሉም አማራ ለአንድ ኢትዮጵያ”</u>*** መሪ ቃሉ ይሆን ዘንድ እንጠቁማለን። ለዚህ ደግሞ በዘረኞችና በአሸባሪዎች ግራ የተጋባውና በስሙ የሚነገደው የትግራይ ሕዝብም ሆነ የኦሮሞ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጎን እንደሆነ ጥርጣሬ አይግባን። ቀደም ሲል የወያኔ/ህወሓት አሁን የኦነግ/ብልጽግና ግፍ ቢያንገፈግፍም በምንም መንገድ ከትግራይና ኦሮሞ ምስኪን ሕዝቦች ጋር ሳይያያዝ ትዕግስት በመላበስ ኢትዮጵያን አድን የ“በቃን!” እንቅስቃሴ ሁሉንም ሕዝብ አቃፊ ይሆን ዘንድ ወጣቱ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል። እጅጉን መናገር የሚቻለው በምንም መልኩ ኦሮሚያ ለብቻ፣ ትግራይ ለብቻ፣ አማራ ለብቻ፣ ሌሎቹም ለብቻ ከቶም! ከቶም! ሀገር ሊሆኑ አይችሉም። ለዚህ የጽንፈኝነት አስተሳሰብ እጅ ከተሰጠ አንጠራጠር የእርስ በርስ እልቂቱ የማያባራ ይሆናል። ጥቂት ወንበዴዎች ሀገር በማሸበራቸውና በአገዛዙ በኩል የሚሰጠው ቁዋት የማይሞላ ሰበብና ማታለያ በመደጋገሙና በማሰልቸቱ አማራው በዘር ተደራጅቶ “በቃን!” ብሎ ቢንቀሳቀስም እልውናው የተያያዘው፣ ህይወቱ ከተፈጠረበትን፣ እትብቱ ከተቀበረበት ምድር ከእምዬ ኢትዮጵያ ጋር ነውና ***<u>“ሁሉም አማራ ለአንድ ኢትዮጵያ”</u>*** መሪ መፈክሩ በማድረግ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የማዳን ግምባር ቀደም ሚናውን ይጫወት ዘንድ እንጠቁማለን።

በኢትዮጵያ ልጆች አማራ ሕዝብ የተጀመረው “በቃን!” እንቅስቃሴ ወደሌሎች ከተሞችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ይዛመት ዘንድ እንቅስቃሴው ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ብሔር/ብሔረሰቦች ወገኖች የትግሉ አካል ይሆኑ ዘንድ ጥሪ ማስተላለፍ ይኖርበታል። “በቃን!” መሪ ቃል ኢትዮጵያን ማዳን ይሆን ዘንድ የትግራይና የኦሮሞ ሕዝቦች እንዲሁም ሌሎች ወገኖች ኢትዮጵያዊነትን ይቀላቀሉ ዘንድ ጥሪ እያስተላለፈ የተጀመረውን እንቅስቃሴ ያለምንም ማመንታት ለኢትዮጵያዊነት ድል ለማብቃት ከታቀደ ሀገርና ሕዝብ ከጎናችሁ እንደሚሰለፍ አትጠራጠሩ። ምክንያቱም በኦነግ/ብልጽግና አካሄድ አማራው ካለቀለት በቀጣዩ ሌሎች ወገኖች በቀላሉ እንደሚደፈሩና እንደሚመቱ ብለውም ወደባሰ ባርነት እንደሚገቡ ተስፋ አድርገዋል የሚል እምነት ስላለን ነው። የወያኔ/ህወሓት የበኩር ልጅ የኦህዲድ/ብልጽግና አገዛዝ እና አጥፊው ሕገ መንግስት ከቶም ሊያበቃ የሚችለው “በቃን!” እንቅስቃሴ ለኢትዮጵያችን አንድነት ለሕዝቧ ደህንነት አድማሱን ሲያሰፋ መሆኑን ደጋግመን እንጠቁማለን።

አማራውን እጅና እግሩን አስሮ የሚያስፈጀው አማራ ዲሞክራቲክ ፓርቲ (አዴፓ) ለአማራው እልቂት ዋነኛ ተጠያቂ መሆኑንም ወጣቱ መገንዘቡ በጣም የሚያኮራ ነው። ከነዚህ አማራው ሲያልቅና ሲፈጅ እንባ ካልወጣቸውና ይልቁንም ያዘነውን አማራ በእስራትና በስቃይ ከቀጡ ከሀዲ ኢህድኖች ከዛም አዴፓዎች ጋር የሞት ትንቅንቅ ማድረጉ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን የ“በቃን!” እንቅስቃሴ ማገናዘቡም፤ የድሎች መጀመሪያ ጠላትን ማወቅ ግንዛቤ ነው የሚለውን ብሂል አረጋግጡዋል። በዚህም ደስታችን ወደር የለውም። “ጠላትማ ምንጊዜም ጠላት ነው መጀመሪያ መግደል አጎብጉዋቢውን ነው” የሚለው የአባቶች መመሪያ አሁን ደርሱዋል።

ዛሬ የሕዝባችንን አእምሮ ኮቪድ 19፣ የኑሮ ውድነትና ረሃብ በተቆጣጠረበት ወቅት ላይ መንደር እየወደመ የሰው ልጅ እየታረደ ከአንድ አካባቢ ራቅ ብሎ መሄድ አስጊ በሆነበት ዘመን ሁኔታውን አይቶ የተጀመረውን የምርጫ ቧልት ውድቅ ማድረግ እንደሚገባ ብልጽግናን አጃቢ ለሆናችሁ ፖለቲከኞች ልናሳስብ እንወዳለን። ምርጫው የተበላ ቁማር ለመሆኑ በየአካባቢው ሕብረተሰብ ላለመመዝገብ ከሚያሳየው ሂደት ግንዛቤ  ልንወስድ ይገባል። ቀደም ሲል በተለያዩ የኢትዮጵያችን ጽሁፎች እንደገለጽነው "ከፈረሱ በፊት ጋሪው" እንዲሉ የጠቅላይ ሚንስትር ዐብይ አገዛዝ ቅንነት ቢኖረው ከምርጫ በፊት ትውልድ ተሻጋሪ ሕዝባዊ ሕገ መንግሥት የሚረቀቅበትና በሕዝብ ተሳትፎ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ መሥራት ነበረበት። የብልጽግና ግብ በኦሮሙማ ግብ የታጀበ እልቂት ነውና ወያኔን ለቀብር ባበቃው የዘረኝነት ሕገ መንግስት ሀገር ሊመራ ሲውተረተር ማድመጥ ተሳነው እንጂ "የቀን ጅብ በግ ላይሆን" ብለን ከጅምሩ ጠቁመናል። ዘረኝነትና የወያኔ/ኢሕዴግ ሕገ መንግሥት እውነት እውነት እንላለን በቅቶታል። በሕዝብ ፍላጎት ለልጆቿ የሆነች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት በአማራው የተለያዩ አካባቢዎች የተለኮሰው የ"በቃን!" እንቅስቃሴ ሕዝባዊ መልክ ይዞ ወደ ሌሎች አካባቢዎችና ከተሞች አዲስ አበባን ጨምሮ ይዛመት ዘንድ አማራው ግምባር ቀደም ፋኖነቱን በማሳየት የሀገር አድን አደራውን መወጣት ይኖርበታል። ከእንግዲህ በምንም መልኩ በመንግሥት በኩል ለሚቀርብ መደለያና የሸንገላ መግለጫ ሳይደናገር በእንቅስቃሴው መግፋት ይኖርበታል ባለድልም የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሆናል። አምባገነኖች ውጥረት ሲበዛባቸው፣ ሲቃ ሲይዛቸው በኢትዮጵያ ስም እየማሉና እየተገዘቱ፣ ያንተኑ ቃል እየተናገሩ ከትግልህ ሊያዘናጉህ የሚያደርጉት ጥረት አዲስ ሳይሆንብህ "በቃን!" እንቅስቃሴ ሕዝባዊ እምቢተኝነት ይላበስ ዘንድ በየትኛውም አካባቢ ያላችሁ ወጣቶች ሀላፊነት አለባችሁ። የደረቀ የእናታቸውን ጡት የሚምጉ ሕጻናት በእናታቸው እቅፍ ላይ መታረድ፣ በእሳት መቃጠል፣ ከነቤታቸው በቦንብ መጋየት ሊያበቃ የሚችለው በከባድ መስዋዕትነት ነውና ***"ሁሉም አማራ ለኢትዮጵያ"*** እንቅስቃሴውን በድል ለመወጣት ቆራጥነቱ ብቻ በቂ ነው። የዐቢይ አህመድ "ኢትዮጵያ አትፈርስም" ተረት ኦሮሚያን የምትመስለዋ ግንጥል ጌጥ ኢትዮጵያን እንጂ ሁሉን እኩል አቀፍ ኢትዮጵያን አለማለቱን ወጣቱ መገንዘብ አለበት ። ድፍን ኢትዮጵያ እድሜ ለጽንፈኛ ወያኔዎችና ኦህዴዶች ተሸርሽራ አሁን ዳር ድንበር ተደፈረ ቢባል ዘራፍ ብሎ የሚወጣ ትውልድ እንዳይገኝ ቅስሙን ቢሰብሩትም በ"በቃን!" ጅምር ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት እንደሚያብብና፣ እንደሚገነባ ሙሉ ተስፋ አለን።

ታሪክ እራሱን ይደግማል እንዲሉ የ1966ቱ "ፋታ ስጡን" ንግግር በዛሬው "እስከ ምርጫው ታገሱን" የሚለው ማፋዘዣ የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት መግለጫ የተጀመረው አማራዊ እንቅስቃሴ የፈጠረው አስደንጋጭ ስጋት ወደ ሌላ እንዳይዛመት የተሰጠ ተማጽኖ ነው። ይህ ማስጠንቀቂያ የአምባገነኖች የተለመደ ጩኸት መሆኑን "በቃን!" እንቅስቃሴ መረዳት ይኖርበታል። ወያኔ/ህወሓት "አከርካሪውን መተነዋል" እያሉ የጨፈሩት፣ የተኩራሩት አማራ ከቶም እንዳልተነካ በቅርቡ ወያኔ/ህወሓትን በመቅበሩ ጦርነት ላይ አማራው ያስመዘገበው ድል ያስበረገጋቸው የኦነግ/ብልጽግና አገዛዞች በዱላና ድንጋይ እንቅስቃሴውን የጀመረውን ቄሮ ገጀራና ቆንጨራ ቢያስታጥቁትም ፍንክች ያላለ አማራ ዛሬ በዘመናዊ መሳሪያና "በአልሞ ተኳሾች" ስናይፐር ጥቃት እንዲደርስበት ቢደረግም፣ ምስኪኑ ገበሬ በጅምላ ቢፈጅም፣ እናቶችና ሕጻናት በዋይታ በእሳት ቢጋዩም የመጨረሻው ድል ኢትይዮጵያዊነት ነውና ለዚህ ደግሞ አማራው ክንዱ እንደፈረጠመ፣ ብሶቱ እንደገነፈለ ያሳየበትን "በቃን!" እንቅስቃሴ አጠናክሮ ኢትዮጵያን ማዳን ይኖርበታል እንላለን። "እየዬ ሲዳላ ነው" እንዲሉ በዐባይ ውኃ ሙሌት ሊሸነገል የታሰበው የዛሬው የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት መግለጫ ለብልጽግና ጊዜ መሸመቻ ነውና ትግሉ ይጠናከር ይፋፋም ዘንድ "በቃን!" እንቅስቃሴ ***"ሁሉም አማራ ለአንድ ኢትዮጵያ"*** መሪ መፈክር አድማሱን ያሰፋ ዘንድ ያለንን ድጋፍና ምክር እንለግሳለን።

**ሁሉም አማራ ለአንድ ኢትዮጵያ!**

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይጠብቅ!!!**

**አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ**

**ሚያዝያ 16 ቀን 2013 ዓ.ም. (April 24, 2021)**

ማሳሰቢያ ፡

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «***ኢትዮጵያችን***» ልሳን በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org , www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin